# ፪ኛ ተሰሎንቄ መልዕክት

# ማጥኛ

በኢትዮጵያዊያን ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተክርስቲያን
የቅዱሳንን ማነጽ አገልግሎት የተዘጋጀ
2010

© Ethiopian Evangelical Baptist Church, 2010
የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተክርስቲያን, ፪፻፻፲
2822 S. Jupiter Road
Garland, TX 75041
214 703 0100
www.eebc-dallas.org

ይህንን የ፪ኛ ተሰሎንቄ ማጥኛ እና ማስጠኛ በከፊልም ሆነ በሙሉ ኮፒ አድርጎ መጠቀም ይቻላል። ይዘቱን ለመቀየር ግን የቤተክርስቲያኑቱን ፈቃድ ከላይ በተሰጠው አድራሻ መሰረት መጠየቅ ያስፈልጋል!

፩. ዳራ (Outline)

I. ሰላምታ (1፡1-2)

ሀ. ከጳውሎስ፣ ከስልዋኖስ እና ከጢሞቴዎስ

ለ. በተሰሎንቄ ላለች የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን

ሐ. ጸጋ እና ሰላም ከእግዚአብሔር

II. የሚያስመሰግን እና የሚያስመካ ሕይወት (1፡ 3-4)

ሀ. የተሰሎንቄ ሰዎች ሕይወት የሚያሰመሰግን ነው (3)። ምክኒያቱም

1. እምነታቸው እያደገ ነው

2. ፍቅራቸው እየበዛ ነው

ለ. የተሰሎንቄ ሰዎች ሕይወት ለነጳውሎስ የሚያስመካ ነው (4)። ምክኒያቱም፡-

1. መከራን በእምነት የታገሱ ናቸው

2. በመከራቸው እና በስደታቸው የጸኑ ናቸው።

III. የክርስቶስን ዳግም ምጻት በማሰብ ለተሰሎንቄ ሰዎች በመከራ እንዲበረታቱ የቀረበ ጥሪ (1፡ 5-10)
ሀ. መከራቸው የእግዚአብሔር ፍርድ እየቀረበ ለመሆኑ ምልክት ነው (5-7)

1. የእግዚአብሔር ፍርድ ሲመጣ አማኞች ለእግዚአብሔር መንግስት ብቁ ሆነው ይቆጠራሉ (5)

2. የእግዚአብሔር ፍርድ ሲመጣ አማኞችን መከራ የሚያሳዩት መከራን ይቀበላሉ (6)

3. የእግዚአብሔር ፍርድ ሲመጣ እግዚአብሔር ለአማኞች እረፍትን ይሰጣል (7)

ለ. ይህ ፍርድ የሚመጣው ኢየሱስ ከሰማይ ሲገለጥ ነው (7-9)

1. በዚያ ቀን የማያምኑት እና አመጻኞች የሆኑት በዘላለም ፍርድ ይቀጣሉ (8)
2. በዚያ ቀን ጌታ በሚያምኑበት ዘንድ ሊከብር እና አማኞቹ ሊገረሙበት ይመጣል (9)
3. ጌታ አማኞችን የሚያከብረው በወንጌል ምስክርነት ስለሚያምኑ ነው (10)።

IV. ለተሰሎንቄ ሰዎች የጳውሎስ ጸሎት (1፡ 11-12)

V. በጌታ ዳግም ምጻት ሰሞን የሚሆኑ ክስተቶች (2፡1-12)

ሀ. የተሰሎንቄ አማኞች ሊረበሹ አይገባም (1-2)

1. የጌታ ምጽት እና የአማኞች መሰብሰብ የተፈጸመ ነገር ነው ብለው መደናገጥ የለባቸውም (1)

2. የሐሰት መምህራን በሚናገሩት እና በሚጽፉት መረበሽ የለባቸውም (2)

ለ. ከጌታ ምጻት በፊት ሊሆኑ የሚገቡ ነገሮች ( 3-12)

1. በመጀመሪያ ክህደቱ እና የአመጽ ሰው ይመጣሉ (3 -5)

2. የአመጽ ሰው አሁን በግልጥ እንዳይሰራ የሚከለክለው አለ (6-7)

3. የአመጽ ሰው በሚገለጥበት ጊዜ ጌታ በዳግም ምጻቱ ያጠፋዋል (8)

4. እንደ ሰይጣን አሰራር የሚሰራው የአመጽ ሰው እውነትን የማይወዱትን ያስታቸዋል (2፡9-12)

VI. ክርስቲያኖች ጸንተው እንዲቆሙ የቀረበ ጥሪ (2፡13 - 3፡5)

ሀ. ለተሰሎንቄ ሰዎች የቀረበ ምስጋና (13-14)

1. እንዲቀደሱ እና እንዲድኑ እግዚአብሔር ስለመረጣቸው (13)

2. የኢየሱስን ክብር እንዲካፈሉ እግዚአብሔር ስለጠራቸው (14)

ለ. የተሰሎንቄ አማኞች ጸንተው እንዲቆሙ ይገባል (2፡15- 3፡5)

1. የተማሩትን እውነት አጥብቀው በመያዝ (2፡15)

2. በእግዚአብሔር እርዳታ በቃል እና በበጎ ስራ (2፡16-17)

3.የእግዚአብሔር ወንጌል እንዲሰራጭ እና እንዲከብር በመጸለይ (3፡1-2)

4.በሚያጸናው እና በሚጠብቀው ጌታ በመታመን (3፡3-5)

VII. ያለ ስርዓት የሚሔዱትን ስነስርዓት እንዲያስይዙ የተሰጠ ማሳሰቢያ (3፡6 - 15)

ሀ. የተሰሎንቄ አማኞች ያለ ስርዓት ከሚሔዱት ሊለዩ ይገባል  (ቁ. 6 - 10)

ለ.   ሥራ ሳይሰሩ በሌላው ላይ ጫና የሚሆኑት ሊወገዙ እና ሊመከሩ ይገባል (ቁ. 11-12)

ሐ.   ያለ ስርዓት የሚመላስ ሰው አግባብ እንዲይዝ የሚደረግበት መንገድ (13-15)

VIII.የመዝጊያ አሳቦች እና ስንብት (3፡16 - 18)

## ጥናት አንድ
## የሚያመሰግን እና የሚያስመካ ሕይወት!

የምንባብ ክፍል፡ 2ኛ ተሰሎንቄ 1፡1-4

የጥናቱ አላማ ፡- በእግዝዚአሔር ፊት የሚያስመሰግን እና የሚያስመካ ሕይወት ሊኖረን የሚችለው፣ በጌታ ያለን እምነት እና ፍቅር እያደገ ሲሔድ እና ክርስትናን በሚፈትኑ ከባድ ሁኔታዎች ውስጥ የሚታገስ እና ጸንቶ የሚቆም ታማኝ ሰዎች በመሆን እንደሆነ በማወቅ የእምነት፣ የፍቅር እና የጽናት ሰዎች እንድንሆን ማሳሰብ።

መግቢያ ፡-

በክርስትና ሕይወት አድጌ ጨርሻለሁ የሚባል ነገር የለም! በዚህ ምድር እስካለን የክርስትና ሕይወት እድገት ከቶ አያልቅም፣ አማኝ አድጌአለሁ፣ ከዚህ በኃላ ምንም አያስፈልገኝም የሚልበት ነጥብ ላይ ከደረሰ በትዕቢት መነፋቱን እና ገና አለማደጉን ያሳያል። ስለዚህም እግዚአብሔር ሁልጊዜ በእምነታችን፣ በፍቅራችን፣ መልካም በማድረግ፣ በጸሎት ሕይወት እንዲሁም በቃሉ ከእለት ወደ ዕለት እንድናድግ ይፈልጋል። እንዲህ ያለው ሕይወት እግዚአብሔር እንዲመሰገን እንዲሁም ለሚያገለግሉንም የሚያኮራ መልካም ሕይወት ነው። በዛሬው ትምህርታችን፣ ይህንን እውነት በመረዳት፣ በእምነት እና በፍቅር እንዲሁም በጽናት እንዴት ማደግ እንዳለብን እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች ፡-

1.በመልዕክቱ የመጀመሪያ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ጸሐፊው ራሱን እና የመልዕክቱን ተቀባዮች ይነግረናል። በዚህ መሰረት
•ጳውሎስ እና አብረውት ያሉት ወንድሞች እንዲሁም የተሰሎንቄ አማኞች ከዚህ ቀደም ይተዋወቁ ነበር ብለህ ታስባለህ?

•እንዴት ሊተዋወቁ እና ደብዳቤ መላላክ ላይ ሊደርሱ ቻሉ? ባለፈው በ1ኛ ተሰሎንቄ ካጠናነው እና ከሐዋሪያት ስራ ምን ማስረጃ ማቅረብ ትችላለህ?

2.በቁ. 1 ላይ ጳውሎስ እግዚአብሔርን "አባታችን" በማለት ይጠራል፣ በዚህ መሰረት

•በጳውሎስ እና በግብረ አበሮቹ እንዲሁም በተሰሎንቄ ሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት ምን አይነት ግንኙነት ነው?

3.በ2ኛ ተሰ 2፡ 2 እና በ 1ኛ ተሰ 1፡1 መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

•በ1ኛ ተሰሎንቄ ተመልክተነው እንደነበረው አምነው ለዳኑ ሰዎች "ጸጋ" እና "ሰላም" ምን ያደርጋሉ?

4.በቁ 3 መሰረት፣ የተሰሎንቄ ሰዎች እምነታቸው እያደገ ስለሆነ እና ፍቅራቸው እየጨመረ ስለሄደ እግዚአብሔርን ያመሰግናል። በዚህ መሰረት

• በ1ኛ ተሰ 1፡2 እና 3 መሰረት እምነት በአማኝ ሕይወት ውስጥ የሚያፈራው ውጤት ምንድን ነው?

•ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች እምነት እያደገ መሆኑን በምን ሊያውቅ ይችላል?

___

___

___

•አንድ አማኝ በጌታ ያለው እምነት እያደገ መሆኑስ በምን ይታወቃል?

___

___

___

•እንደገና በ1ኛ ተሰ 1፡ 2-3 ባለው ፍቅር በአማኝ ውስጥ መኖሩ የሚታወቀው በምንድን ነው?

___

___

___

•በዚህ መሰረት አንድ አማኝ ፍቅሩ እያደገ ነው ወይንም እየበዛ ነው የምንለው ምን ሲሆን ነው?

___

___

___

5.በተሰሎንቄ የሚገኙ አማኞች የመጀመሪያው መልዕክት በተጻፈላቸው ጊዜ ሁለቱም እምነትም ሆነ ፍቅር እንደነበራቸው ከ1ኛ ተሰ 1፡1-2 ባለው አይተናል፤ ሆኖም ግን አሁን እምነታቸው እና ፍቅራቸው ይበልጥ መጨመሩ ዛሬ ለእኛ የሚያስተምረን ምንድን ነው?

___

___

___

___

6.በቁ. 4 መሰረት ጳውሎስ ከአብያተ ክርስቲያናት መካከል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን እንዲመካ እና እንዲደሰት ያደረጉት ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው? (አዲሱ መደበኛ ትርጉምን ይመልከቱ!)

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

7.በቁ. 4 ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች በመከራ መጽናታቸውን ይነግረናል።
•ከዚህ ቀደም ባጠናነው በ1ኛ ተሰሎንቄ ውስጥ እነዚሁ ሰዎች በመከራ እንደጸኑ የሚናገር ክፍል ታስታውሳለህ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

•በዚሁ ክፍል መሰረት መጽናት ምንድን ነው? አንድ ሰውስ እንደጸና የሚታወቀው በምንድን ነው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

•በመከራ ስለሚጸና ሰው ያዕ 5፡10-11 ያለው ክፍል የሚሰጠን ምሳሌ ማንን ነው? እንደዚህስ የሚጸና ሰው ምን ይባላል?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

8. እንግዲህ ጳውሎስ ስለ ተሰሎንቄ ሰዎች እግዚአብሔርን ያመሰገነበትን እና ራሱም ጳውሎስ በነዚሁ አማኞች የኮራበትን ነጥቦች በማየት፣ የሚያስመሰግን እና የሚያኮራ የክርስትና ሕይወት ምን አይነት ነው?

9. ዛሬ አንተስ እንደዚህ ያለ ሕይወት እንዲኖረን እኛ ክርስቲያኖች በሕይወታችን መጨመረ ያለብን ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? (እባክዎን በእምነት እና በፍቅር ማደግ የሚል ድፍን መልስ አይስጡ! በተግባር ሊተረጎም የሚችል ግልጽ ምሳሌ ይስጡ!)

*መደምደሚያ ፡-*

በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች የመጀመሪያው መልዕክት በተጻፈላቸው ጊዜ ምንም እምነታቸውን በተግባር እና በመልካም ስራ፣ ፍቅራቸውንም ለሌላው በመድከም ይገልጹ የነበሩ ብርቱ የፍቅር እና የእምነት ሰዎች የነበሩ ቢሆኑም፣ የክርስትና ዕድገታቸው አልቆመም። ይልቁንም ይህ ሁለተኛው የጳውሎስ መልዕክት በተጻፈላቸው ጊዜ እምነታቸው እና ፍቅራቸው ከፊት ይልቅ ከመጨመሩ ሌላ፣ በጌታ የሚደርስባቸውን መከራም በእምነት እና በትዕግስት መወጣታቸውን ቀጥለዋል። ልክ እንደነዚህ ሰዎች ሕይወት ክርስትና የማደግ እና የመብዛት ሕይወት ነው። ታዲያ እኛስ ሕይወታችን እያደገ እና እየተለወጥ ከትላንቱ ዛሬ እየተሻልን ይሆን? ለማድግስ ምን እያደግን ነው?

**ጥናት ሁለት**
**የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ**

የምንባብ ክፍል፡ 2ኛ ተሰሎንቄ 1፡5 - 12

የጥናቱ አላማ ፡- እግዚአብሔር ቅን እና ጻድቅ ፈራጅ እንደሆነ በማወቅ ፍትህ ተጓድሎብኛል በምንለው ሁኔታ ውስጥም እንኳ የእግዚአብሔርን ስም እያስከበርን እንድንኖር ማሳሰብ።

*መግቢያ ፡-*

የምንኖረው ፍትህ በጎደለበት አለም ውስጥ ለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልገንም - በየቀኑ የምናየው ሐቅ ስለሆነ። በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔርን ፈርቶ እና ጌታን አስከብሮ መኖር ከባድ እና አስቸጋሪ ይመስላል። ሆኖም ግን፣ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጌታ ሁሉን ወደ ፍትህ የሚያመጣበት ቀን አለው። ስለዚህም ፍትሕ የሌለበት እና ፍርድ የተጓደለ በሚመስልበት ቦታ እና ሁኔታ ውስጥም እንኳን የተዛባን ፍትህ የሚያቀና ፈራጅ እና ጌታ እንዳለ በማወቅ ክርስቲያን ሁልጊዜ ስለ እግዚአብሔር መኖር ይችላል። በእርግጥም እግዚአብሔር በፍትሕ የሚበይን ስለሆነ፣ አንድ ቀን እንደዚህ ስለ ስሙ ጸንተው የሚኖሩትን ያከብራል እንዲሁም ደግሞ በእነሱ መካከል ጌታ ይከብራል።

*የመወያያ ጥያቄዎች ፡-*

1. ባለፈው ሳምንት፣ ከ 2ኛ ተሰ 1፡1-4 ባለው የተመለከትነው እና የተማርነው ምንድን ነው?
2. በቁ 5 ላይ "ስለ እርሱ ደግሞ መከራን ለምትቀበሉለት" በማለት በተሰሎንቄ ያሉት አማኞች መከራን እየተቀበሉ እንዳሉ ይገልጽልናል።
• በዚህ ክፍል መሰረት መከራን የሚቀበሉት ለማን ነው? "ስለ እርሱ መከራን ስለምትቀበሉለት" ሲል ስለ "እርሱ" የሚለው ማንን (ምንን) ነው? መልሱን ለማግኘ አዲሱ መደበኛ ትርጉምን ይመልከቱ!

•በዚሁ ክፍል ላይ "ይህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ ምልክት ነው" ሲል እግዚአብሔር ቅን ፈራጅ የመሆኑ ምልክት ምንድን ነው?

•በዚሁ በቁ. 5 ላይ እግዚአብሔር ቅን ፈራጅ ስለሆነ በተሰሎንቄ ለእግዚአብሔር መንግስት መከራን እየተቀበሉ ላሉት አማኞች እግዚአብሔር የሚያደርግላቸው ምንድን ነው?

3.በቁ. 6 እና 7 መሰረት እንደ ጻድቅ ፈራጅነቱ እግዚአብሔር የሚያደርጋቸው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

4.እግዚአብሔር ለኃጢአተኞቹ መከራን በመስጠት፣ ለሚያኑበት እና ዋጋን ለሚከፍሉት እረፍትን መስጠቱ የእግዚአብሔርን ጽድቅ የሚያሳየው እንዴት ነው?

5.በዚህ ክፍል ውስጥ ጌታ "በእሳት ነበልባል" እንደሚገለጥ መግለጽ ለምን አስፈለገው ብለህ ታስባለህ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

6.ከቁ. 8 -10 ጌታ በሚመጣበት ጊዜ ስለሚቀጡት እና  በዚያ ጊዜ ጌታ ስለሚከብርባቸው ሁለት አይነት ሰዎች ይናገራል።

•በቁ 8 መሰረት ጌታ የሚቀጣቸው ሰዎች እነማነ ናቸው፣ የሚቀጣቸውስ ለምንድን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

•በቁ. 9 መሰረት ጌታ ሲመጣ የሚከብርባቸው እነማን ናቸው፣ እነሱንስ የሚያከብርበት ምክኒያቱ ምንድን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

•በዚህ ክፍል መሰረት ለመዳን እና ለመኮነን ዋነኛው ምክኒያት ምንድን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

7.በቁ 9 ላይ ስለ ጌታ መምጣት ሲናገር "በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ ሊገረም ሲመጣ" ይላል። ጌታ በሚያምኑ ሰዎች በእውነት ይገረማል ወይስ ሌላ ትርጉም አለው? (የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ካለህ ትርጉሙን አወዳድር)።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

8.በቁ. 11-12 ባለው ጳውሎስ ደብዳቤ ለሚጽፍላቸው ሰዎች ይጸልያል።
- በዚህ መሰረት ጳውሎስ ስለነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ያቀረባቸው ሁለት ርዕሶች ምንድን ናቸው? (አዲሱ መደበኛ ትርጉምን ያወዳድሩ)

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

9. ስለ እግዚአብሔር መንግስት በግፍ መከራን እየተቀበሉ ላሉት አማኞች እውነተኛውን ፍትሕ እግዚአብሔር ወዲያውኑ ሊሰጣቸው ሲችል፣ ገና ወደፊት ጌታ ሲመጣ እንደሚፈረድላቸው መንገር ያስፈልጋል?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

10. ከዛሬው ትምህርት በመነሳት እግዚአብሔር የፍትሕ አምላክ ከሆነ፣ ጌታ እስኪመጣ ድረስ አማኞች ማድረግ ያለብን ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

መደምደሚያ :-
እግዚአብሔር ጻድቅ እና የፍትሕ አምላክ ነው፤ ሆኖም ግን እግዚአብሔር ብያኔ ለመስጠት የሚቸኩል አምላክ አይደለም! በዚህ ምድር እያለን ፍትህ በተጓደለበት አይነት ሁኔታ ስለ ጌታ ተበድለን ልንኖር የምንችልበት ብዙ አጋጣሚ አለ። ጌታ ወዲያውኑ በአንድ ጊዜ መልስ የማይሰጥበት እና እግዚአብሔር ጻድቅ መሆኑ  የምንጠረጥርበት አያሌ ጊዜዎች ይኖራሉ። እውነታው ግን እግዚአብሔር ጻድቅ ነው! አንድ ቀን ጌታ ሲመጣ ለሁሉ እንደየስራው የሚፈርድበት ጊዜ አለ። ስለዚህም እንደ እግዚአብሔር ሰዎች ጌታ ቀን እንዳለው በማስተዋል ዛሬን በቅንነት እና በጽድቅ ስለ እግዚአብሔር መንግስት እንድንኖር ይጠበቅብናል።
ጥናት ሦስት
አትረበሽ !

# የምንባብ ክፍል፡ 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡1-12

የጥናቱ አላማ ፡- የጌታ ቀን ገና ሊመጣ እንዳለ በማወቅ፣ እና ጌታ እስኪመጣ ድረስ እውነትን የሚቀበሉ እና በእውነት ጌታን የሚከተሉትን የሚያሰጋቸው ከቶ እንደለለ በማወቅ ተረጋግተው እንዲኖሩ ማሳሰብ።

መግቢያ ፡-

መታወክ፣ መረበሽ እና መደናገጥ የሰው ባሕርይ ነው። ሆኖም ግን በጌታ ላሉ ይህንን ሁሉ ሊለውጥ የሚችል ተስፋ አለ - ያም የጌታ ዳግም ምጻት ነው። ጌታ በምድር በነበረበት ጊዜ ዳግም እንደሚመጣ ሲያስተምር፣ "ልባችሁ አይታወክ" ዮሐ 14፡1 ብሏል፣ ጳውሎስ በዚሁ ርዕስ መልዕክት ሲጽፍ "በዚህ ቃል እርስ በእርሳችሁ ተጽናኑ" 1ኛ ተሰ 4፡18 እንዲሁም "ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ" 1ኛ ተሰ 4፡13 ሲል መክሯል። በዚህ መልዕክት ደግሞ ስለ ጌታ መምጣት በተመለከተ በሚሰጥ ሐሳዊ ትምህርት ሁሉ አማኝ ሊደነግጥ እና ሊረበሽ ከቶ አይገባም። የጌታ መምጣት ለአማኝ ደስታ እና ተስፋ ነው! በእርግጥ ከጌታ መገለጥ  በፊት በሐሰተኛው ክርስቶስ መገለጥ ምክኒያት በሚደረጉ ድንቆች እና ተአምራት የሚስቱ እና እግዚአብሔር ኋላ የሚፈርድባቸው ቢኖሩም፣ የሚስቱት እና የሚጠፉት የማያምኑት እና በአመጻ ደስ የሚላቸውን እንጂ አማኞችን አይደለም - ጌታ የራሱ የሆኑትን አሳልፎ አይሰጥምና። ስለዚህ ጌታ ዛሬም መጣ ነገ አሳቾች መጡም ቀሩ … አማኝ ግን ባለው ተስፋ ደስ ሊሰኝ እና ተረጋግቶ ሊኖር ይገባዋል።

የመወያያ ጥያቄዎች ፡-

1.ባለፈው ጊዜ 2ኛ ተሰ 1፡5 - 12 ያለውን በተመለከትን ግዜ ስለ ጌታ ምጻት እና ስለ እግዚአብሔር ቅን ፈራጅነት የተማርነው ምንድን ነው?

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

2. በቁ. 1 እና 2 መሰረት በተሰሎንቄ ያሉትን አማኞች እንዲታወኩ እና እንዲረበሹ ያደረጋቸው ነገር ምንድን ነው?

•የሐሰት አስተማሪዎች ያስተምሩ የነበሩት ነገር ምንድን ነው?

___

___

___

•የስህተት ትምህርታቸውንስ ከየት እንዳመጡት ነው የሚናገሩት?

___

___

___

3.የጌታ ቀን እና የጌታ መገለጥ ከዚህ በፊት የሆነ ነገር ከሆነ የተሰሎንቄን ሰዎች ሊረብሻቸው የሚችለው ነገር ምንድን ነው?

___

___

___

4.በቁ. 3 መሰረት ከጌታ መገለጥ በፊት "ክህደቱ" እና "የአመጽ ሰው" እንደሚመጡ ይናገራል።

•በዚህ መሰረት የሚመጣው የምን ክህደት ነው ብለህ ታስባለህ?

___

___

___

•ይመጣል የተባለውስ "የአመጽ ሰው" በዚህ ባነበብነው ክፍል ውስጥ ሌላ ምን ምን ስሞች ተሰጥቶታል?

___

___

___

5.	በቁ 4 ላይ በተጻፉት ነገሮች መሰረት፣ ይህ "የአመጽ ሰው" ማን ነው? ማንነቱን የሚገልጹ ምን ምን ነገሮች አሉ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

6.	በቁ. 6 ላይ እንደምናየው ይህ የአመጽ ሰው አሁን እንዳይገለጥ የሚከለክለው አለ! ጳውሎስ ይህ የሚከለክለውን ነገር ግልጽ አድርጎ ባያስቀምጠውም፣ ይህ የሚከለክለው ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

7.	በቁጥር 7 እና 8 መሰረት ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ሐሰተኛው ክርስቶስ የሚገለጠው መቼ ነው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

8.ሀሳዊው ክርስቶስ በግልጽ ተገልጦ ማሳት የሚችልበት ጊዜ እስከሚመጣ ድረስ አሁን እንዴት ነው እየሰራ ያለው?

•አሁን ባለንበት ዘመን የሐሰተኛው ክርስቶስ አሰራር በምስጢር እየተካሄደ ነው ያለው ብለህ ታምናለህ? ከሆነ ምን አይነት ማስረጃዎች ማቅረብ ትችላለህ?________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

9.በቁ. 9 እና 10 መሰረት፣ የሐሰተኛው ክርስቶስ ዛሬ በድብቅ የሚሰራውም ሆነ ወደፊት በግልጽ እና በድፍረት የሚያደርጋቸው ነገሮች በሰይጣናዊ አሰራር የሚደረጉ ናቸው።

•እንደ ክርስቲያን ዛሬ ይህንን በድብቅ የሚሰራውን የክፉ አሰራር ከመጸለይ እና ቃሉን ከማንበብ ሌላ ልንቃወመው የምንችለው እንዴት ነው ብለህ ታስባለህ? ( ኤፌ 6፡10 -20፣ ያዕ 4፡7 ምን አሳቦችን ሊሰጡ ይችላሉ ብለህ ታስባለህ?)

---

---

---

10.በቁ. 9 እና 10 መሰረት ሃሰተኛው ክርስቶስ የሚያስተው ማንን ነው የሚያስተውስ ምን አይነት ስልት በመጠቀም ነው?
•ከእንደዚህ አይነቱ አደገኛ አሳች ለመዳን እና ለማምለጥ ዛሬ አማኝ ማድረግ ያለበት ነገር ምንድን ነው ትላለህ?

---

---

---

11.በቁ. 11 እና 12 ላይ እንደምናየው፣ አንዳንዶች እንዲስቱ እግዚአብሔር ራሱ በሓሳዊው አሰራር እንዲያምኑ እንደሚተዋቸው ይነግረናል።
•እግዚአብሔር  አንዳንዶች የስህተትን አሰራር እንዲቀበሉ እና እንዲጠፉ የሚፈቅደው ለምንድን ነው?

---

---

---

•እነዚህ የሚስቱት ሰዎች ከሌላው የሚለያቸው ምንድን ነው?

---

---

---

12.እስካሁን ባየነው በሐሰተኛው ክርስቶስ መምጣት እና በቁ 3 ላይ ባየነው "በክህደቱ" መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

13.የሀሰትኛው ክርስቶስም ሆነ የጌታችን መገለጥ ሊያስፈራ እና ሊያስደነግጥ የሚገባው ማንን ነው?

•ለአማኝስ የጌታ መምጣት ምንድን ነው? (ዮሐ 14፡1፣ 1ኛ ተሰ 4፡13 እና 18 እንዲሁም 2ኛ ተሰ 2፡1-2 ያሉት እውነቶች ለአማኝ የሚመከሩት ምንድን ነው?)

*መደምደሚያ ፡-*

*ክርስትና የተስፋ ሕይወት እንጂ የማዘን፣ የመቆዘም እንዲሁም ተስፋ የመቁረጥ ሕይወት አይደለም። የጌታ መምጣት ለአማኝ ደስታ እንጂ የመደንገጫ እና የመታወኪያ ምክኒያት ሊሆን አይችልም። በዕርግጥ የጌታ ምጻት እንዲህ በቀላይ የሚሆን አይሆንም፣ የሚያስት በድንቅ እና በተአምራት እንዲሁም በአመጽ ስለሚገለጥ። ቢሆንም ግን ይህ ሁሉ በጌታ ያሉትን ከቶ አያገኛቸውም - ታማኝ አምላክ ይሰውራቸዋልና። ስለዚህ ክርስቲያን በተለይም የጌታን ምጻት በተመለከተ ሊጽናና እና ሊደሰት እንጂ ከቶ ሊታወክ እና ሊረበሽ አይገባም።*

## ጥናት አራት
## *ጽንተህ ቁም!*

የምንባብ ክፍል፡ 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13 -3፡5
የጥናቱ አላማ ፡- እውነትን ባለመቀበል በስሕተት እንደሚጠፉት ሳይሆን፣ በእውነት ቃል፣ በመልካም ስራ እና ንግግር እንዲሁም በጸሎት እና ጌታን በመታመን እንድንጸና ለማበረታታት

*መግቢያ ፡-*

ክርስቲያን ለክብር እና ለተስፋ የተጠራ የታደለ ሕዝብ ነው። ሆኖም ደግሞ እንደታደለ ሕዝብ ደግሞ መኖር ይጠበቅበታል። በጌታችን እና በመድሕኒታችን በኢይሱስ ክርስቶስ ባለማመን እና ለእርሱ ባለመታዘዝ የሚኖሩት ለጥፋት እና ለስህተት ሲጋለጡ፣ የራሱ የሆኑትን ግን ጌታ ከክፉ እየሰወረ ወደ ክብር ይመራቸዋል። ስለዚህም የእግዚአብሔር የሆኑት ለክብር እንደተጠራ ሰው ሊኖሩ እና በተማሩት እና ባወቁት እውነት በጸናት እዲኖሩ ይገባል። በዛሬው ጥናታችን፣ እግዚአብሔር እንደዚህ ለክብር ከጠራን፣ እኛ ደክሞ በተጠራንበት መጽናት እንዳለብን እንማራለን።

*የመወያያ ጥያቄዎች ፡-*

1.ባለፈው ጥናታችን የተማርነው ምንድን ነው?

____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
________

2.ባለፈው ጥናታችን መሰረት፣ ሃሰተኛው ክርስቶስ የሚያስታቸው እና እግዚአብሔርም እንዲስቱ የሚተዋቸው ሰዎች እንዴት ያሉትን ሰዎች ነው?

____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________

3.በዛሬው ጥናታችን  በቁ. 13 እና 13 መሰረት ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ተሰሎንቄ ሰዎች የሚያመሰግንበት ሁለት ምክኒያቶች ምንድን ናቸው?
•"መርጧችኋል" እና "ጠራችሁ" በሚሉት ቃላት መካከል ያሉት ልዩነት ምንድን ናቸው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

•የተሰሎንቄ ምዕመናን የተጠሩት ለምንድን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

•የተሰሎንቄ ምዕመናን የተጠሩት ለምን አላማ ነው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

4.በቁ. 15 ላይ ጸንተው እንዲቆሙ ያዛል።
•ጸንቶ መቆም ማለት ምን ማለት ነው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

•በዚሁ ክፍል መሰረት፣ በምን እና በምንድን ነው ጸንተው እንዲቆሙ ይታዘዙት?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

•በቃል እና በመልዕት በተማሩት ወግ (የክርስትና ሕይወት) እንዴት ነው ጸንተው መቆም የሚችሉት?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

5.በቁጥር 16 እና 17 የተሰሎንቄን ሰዎች እግዚአብሔር በምን እና በምን እንዲያጸናቸው ነው ጳውሎስ የሚጸልየው?

• በቃል እና በኑሮ እንዴት ነው መጽናት የሚቻለው? (1ኛ ጢሞ 4፡11-12 የሚሰጥህ ፍንጭ አለ?)

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

6.በም 3፡ 1-2 ባለው መሰረት ወንጌል እንዲሰራጭ እና ተቀባይነት እንዲኖረው ክርስቲያኖች ሊጸኑበት የሚገባው ሌላ ነገር ምን አለ ብለህ ታስባለህ?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

7.በቁ 3 ከሰው ጥረት ሁሉ በላይ ሰውን ሊያጸናው የሚችለው ጌታ እንደሆነ ይነግረናል።

•ጌታ ሰውን የሚያጸና ከሆነ ከሰው የሚጠበቅ ነገር አለ ብለህ ታስባለህ? (ቁ. 4ን በመመልከት ሰው ማድረግ ያለበትን አብራራ)።

8. በዛሬው ጥናታችን ሰው ጸንቶ ሊቆምበት የሚገባባቸው ነገሮ ምን አሉ?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

*መደምደሚያ ፡-*

ክርስቲያን ለመልካም ሕይወት እና ክብር ተጠርቷል። ስለዚህም በተሰጠው ክርስቲያናዊ ሕይወት፣ እንዲሁም ትምህርት ሊተጋ፣ በጸሎት፣ በቃል እና በመልካም ስራ ሁሉ ጸንቶ የሚቆም እንዲሆን ይገባል። የከበረው ሕዝብ እንደከበረ ሕዝብ እንዲመላለስ ይጠበቅበታል።

## ጥናት አምስት

## ያለ ስርዓት የሚሔዱትን ስርዓት አስይዟቸው!

## የምንባብ ክፍል፡ 2ኛ ተሰሎንቄ 3፡6 - 18

የጥናቱ አላማ ፡- ክርስቲያኖች ራሳቸውን ለመቻል ቀን እና ሌሊት ሊደክሙ እና ከአቅም በላይ በሆነ ጉዳይ ካልሆነ በቀር በማንም ላይ ጫና ከቶ ሊሆኑ እንደማይገባ ማሳሰብ።

መግቢያ ፡-

አለመስራት፣ ቀን እና ሌሊት እጅ አጣምሮ መቀመጥ እጅግ ነውር ነው። ሰው የተፈጠረው እንዲሰራ እንዲያስተዳድር - ከፍጥረት ጊዜ ጀምሮ። ሆኖም ግን ይህንን ስርዓት ጥሶ ስራ ፈት መሆን በጌታ ዘንድ የሚያስጠይቅ መሆኑ ግልጽ ሆኖ ሳለ ይልቅ ደግሞ በየሰዉ ጉዳይ መግባት እንዲሁም የሌላውን የድካም ዋግ እየተሻሙ በሰው ላይ ሸክም መሆን የባሰ ጥፋት ነው። ክርስቲያን በሰው ጫና እንዲሆን ሳይሆን በገዛ እጆቹ እየደከመ ለሌለው እንዲያካፍል የተጠራ ሕዝብ ነው (ኤፌ 4:24)። በዛሬው ጥናታችን በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ሥራ ፈት ሰዎች የተሰጣቸውን ማሳሰቢያ በመመልከት እና ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያሉትን ሰዎች እንዴት መቅጣት እንዳለባት የተጻፈውን በማየት ጌታ ከእኛ የሚፈልገውን እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች ፡-

1.ባለፈው ሳምንት ያጠናነው ነገር ምን ነበር?

______________________________

______________________________

______________________________

2.በቁ 6 ላይ ጳውሎስ ያለ ስርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ አማኞች እንዲለዩ ያዛል። በዚህ መሰረት

•ያለ ስርዓት" መሄድ ማለት ምን ማለት ነው?

______________________________

______________________________

______________________________

•እንደዚህ ካለው ሰው ተለዩ ሲል ምን ማለቱ ነው? እንዴትስ ነው የሚለዩት? (ቁ. 14 የሚሰጥህ ፍንጭ አለ?)

______________________________

______________________________

______________________________

3.በቁ. 6 ላይ እንደገና እነ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የተውላቸው ወግ እንዳለ ይናገራል።

•በዚህ መሰረት "ወግ" ምንድን ነው?

______________________________

______________________________

______________________________

•ቁ. 7 እና 8ን በማስደገፍ እነ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የተውላቸው ወግ (ክርስቲያናዊ ስርዓት) ምን ነበር?

______________________________

______________________________

______________________________

4.በቁ. 8 መሰረት እነ ጳውሎስ ምንም አገልጋይ ቢሆኑ እና ቀለባቸውን ከተገልጋዮቹ መቀበል ቢችሉም፣ ቀን እና ሌሊት እየሰሩ የዕለት ወጪአቸውን ይሸፍኑ የነበረው ለምድን ነው?

•ይህስ ሰወችን በቃል ብቻ ከማስተማር በሕይወት ምሳሌ በመሆን ማስተማር የተሻነ እንደሆነ ያሳያል ብለህ ታስባለህ? እንዴት?

5.በቁ. 10 መሰረት በሕይወታቸው ምሳሌ እየሆኑ ከማስተማር ባሻገር፣ ሌላ በምን መንገድ ያስተምሯቸው ነበር?
•በዚህ ክፍል መሰረት ሳይሰሩ መብላት ነውር የሆነው ለምንድን ነው?

•ዛሬ ባለንበት ዘመን ሳይሰሩ መብላት የሚፈልጉ ሰዎች ይኖራሉ ብለህ ታስባለህ? አጋጥሞህ የሚያውቅ ከሆነ ለሕብረቱ አካፍል።

6. ጳውሎስ በቁ. 11 መሰረት ይህንን ትምህርት አጥብቆ በቃልም በሕይወትም እንዲያስተምር እንዲሁም እንደዚህ ደብዳቤ እንዲጽፍ ያስገደደው ለምንድን ነው?

7.በቁ. 11 መሰረት እነዚህ ሰዎች ስራ ፈት ከመሆናቸው ሌላ የሚያደርጉት ነገር ምንድን ነው?
• እነዚህ ግለሰቦች ሥራ በመፍታታቸው እና በሰው ጉዳይ በመግባታቸው መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

•በአዲስ ኪዳን በኤፌ 4፡28 መሰረት ሳይሰሩ ሌላው የድካመበትን መሻማት ጥፋት የሚሆነው ለምድን ነው?

በቁ 12 ላይ ጳውሎስ በእንደዚህ አይነት ስርዓት አልበኝነት የሚመላለሱት ሰዎች ሥራ ሠርተው
8.የራሳቸውን ወጪ እንዲሸፍኑ ያዛል።
•	በቁ. 14 መሰረት ለዚህ ስርዓት የማይገዙትን ሰዎች ቤተክርስቲያን እና ምዕመኖቿ ማድረግ ያለባቸው ምንድን ነው?

•የቤተክርስቲያን ሰዎች እንዲህ ካለው ሰው ጋር መተባበራቸውን ማቆም የሚችሉት በምን አይነት መልኩ ነው? (ግለሰቡም ማናገር አይቻልም ማለት ነው?)

•እንደዚህ ያለው ግለሰብ "እንዲያፍር" መደረግ ያለበት ለምንድን ነው?

9.በቁ. 15 መሰረት ያለ ስርዓት ለሚሄደው ሰው መደረግ ያለበት ጥንቃቄ ምንድን ነው?

__________________________________________________________________
__________________________________________________________________
__________________________________________________________________
__________________________________________________________________
________

10.ከዛሬው ትምህርት ምን ተማርክ?

__________________________________________________________________
__________________________________________________________________
__________________________________________________________________
__________________________________________________________________
________

መደምደሚያ ፡-

ክርስቲያን ትጉ ሰራተኛ እንዲሆን ይጠበቅበታል። እግዚአብሔር ሰውን በመጀመሪያ ሲፈጥረው የሰጠው አንደኛው ነገር ሥራ ነው። አለመስራት ነውር ነው! ካለመስራት አልፎ ደግሞ በሰው ጉዳይ መግባት እና ሌላው የደከመበትን መካፈል እጥፍ ነውር ነው። ክርስቲያን ሌላው የደከመበትን የሚዘርፍ ሳይሆን፣ ራሱን ችሎ ያጣውን እና የተቸገረውን የሚደግፍ ትጉ ሰው ነው። ስለዚህም እኛ እንደ ክርስቲያን በዚህ አይነት ሕይወት ልንመላለስ የሚገባን ሲሆን፣ ያለ ስርዓት የሚሄዱትን እና ይህንን ወግ የሚጥሱትን ወቅሰን እና ገስጸን ልናቀናቸው ይገባናል።